

# የኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲቲዩት (IRI)/ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲቲዩት (NDI) የ2013 የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮ - የምርጫ ምልከታ

ሰኔ 2 ቀን 2013 ዓ.ም.

# መግቢያ

ኢትዮጵያ ሰኔ 14 ቀን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ ታከናውናለች። ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲቲዩት እና ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲቲዩት የምርጫውን ስነ ምህዳር በተመለከተ ለኢትዮጵያ ዜጎች እና ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ከወገንተኝነት የጸዳ እና ትክክለኛ ግምገማ ለማቅረብ እና ለዴሞክራሲያዊ ምርጫ የተቀመጡ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ መስፈርቶችን መሰረት ያደረጉ እና ከኢትዮጵያ ሕግ ጋር የሚጣጣሙ ገንቢ ምክረ-ሀሳቦችን ለማቅረብ ውስን የምርጫ ምልከታ ተልዕኮ በጋራ በማከናወን ላይ ይገኛሉ። በአሁኑ ወቅት ያለው ዓለም አቀፍ የጤና ቀውስ በፈጠራቸው ውስንነቶች የተነሳ ተልዕኮው በመከናወን ላይ የሚገኘው ገለልተኛ እና ከወግተኝነት የጸዱ ግምገማዎችን ለማከናወን በዓለም አቀፍ የምርጫ መታዘብ መርሆዎች ድንጋጌ (Declaration of Principles for International Election Observation) በተቀመጡት ደንቦች እና በአፍሪካ ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎች የሚመሩባቸውን መርሆዎች የሚመለከተውን የአፍሪካ ህብረት ድንጋጌ (the African Union Declaration on the Principles Governing Democratic Elections in Africa) ጨምሮ ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው አህጉራዊ ሰነዶች መሠረት የርቀት ተሳትፎ ዘዴን በመጠቀም ነው።

ይህ የምርጫ ምልከታ የቅድመ ምርጫ ስነ-ምህደሩን እና ለምርጫው የሚደረጉ ዝግጅቶችን የተመለከተ ትንተና ከቀረበበት እና ግንቦት 5 ቀን ከወጣው የኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲቲዩት/ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲቲዩት የርቀት የቅድመ ምርጫ ግምገማ ልዑካን ቡድን (VPEAD) ሪፖርት የቀጠለ ነው። ጋዜጣዊ መግለጫው እና ሪፖርቱ በተመሳሳይ ቅደም ተከተል የናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲቲዩት እና የኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲቲዩት ድረገጾች ላይ ይገኛሉ። ይህ ወቅታዊ መረጃ ከሚያዝያ 18 እስከ ግንቦት 23 ቀን 2013 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከፍተኛ ተወካዮችን፣ የመንግስት መሥሪያ ቤቶችን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን፣ መገናኛ ብዙሀንን፣ የዜጋ ምርጫ ታዛቢዎችን እና የዲፕሎማሲውን ማህበረሰብ ጨምሮ ከበርካታ የተለያዩ የምርጫ እና የፖለቲካ ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ጥልቀት ያላቸው የርቀት ቃለ መጠይቆችን መሠረት ያደረገ እንዲሁም ሁለቱም ተቋማት በኢትዮጵያ ላይ ያላቸውን ዕውቀት እና ግንኙነቶች ግብዓት ያደረገ ነው። ተልዕኮው የርቀት ዘዴን በመጠቀም የተከናወነ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የምልከታችን የስፋት ወሰን ውስን ነው እንዲሁም ሪፖርቶቻችን አጠቃላይ የምርጫ ሂደቱን በተመለከተ ድምዳሜዎችን የሚያስቀምጡ አይደሉም።

የኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲቲዩት/ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲቲዩት ጥምር ልዑካን ቡድኑ "ግንቦት 28 ይካሄዳል ተብሎ ቀን የተቆረጠለት የኢትዮጵያ የ2013 ምርጫ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተደረጉ የህግ ማሻሻያዎችን መሠረት በማድረግ በአገሪቱ ውስጥ ሁሉን አቀፍ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አስተዳደርን ለማስፈን የሚያስችል መልካም ዕድል ሊፈጥር ይችላል የሚል ተስፋ አለ። ሆኖም በስፋት የሚስተዋሉ የፀጥታ ችግሮችን እና የብሔር ማንነትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችን፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከሚከናወኑ የእጩዎች እና የመራጮች ምዝገባ ሥነ-ሥርዓቶች ጋር የተያያዙ መዘግየቶችን፣ አንዳንድ የክልል መንግስታት ደካማ የሆነ ትብብር ማሳየታቸውን፣ ሰፊ የህዝብ ድጋፍ ያላቸው በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከምርጫ ሂደቱ ራሳቸውን ማግለላቸውን እና እናገላለን የሚል ማስጠንቀቂያ መስጠታቸውን፣ እንዲሁም ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ የተፈጠረውን የህዝብ ጤና ቀውስ ጨምሮ አዳጋች የሆኑ የተለያዩ ጉልህ ችግሮች መኖራቸው መራጮች እና ፓርቲዎች በሂደቱ ውስጥ ለመሳተፍ ባላቸው አቅም ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድር እና በዚህም ተዓማኒነት ያለው ምርጫ የመከናወኑን ዕድል እንዳያጠበው ያሰጋል። በመሆኑም ከምርጫ ቀን አስቀድሞ በሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚከወኑ ሁነኛ እና የተቀናጁ ጥረቶች ትርጉም ያለው ምርጫ ለማካሄድ እና ከምርጫው ባሻገር ለብሄራዊ እርቅና ለዴሞክራሲያዊ ዕድገት መሰረት ለመጣል አስፈላጊ ግብአቶች ናቸው።" በማለት ገልጿል።


## ፖለቲካን የተመለከተ ወቅታዊ መረጃ፡-

ሰኔ 14 ቀን የሚከናወነው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫ[1] ወታደራዊ ያልሆነ አገዛዝ ወደ ሀገሪቱ ከተመለሰ ወዲህ በኢትዮጵያ የሚከናወነው ስድስተኛው ምርጫ ቢሆንም እ.ኤ.አ. በ2010 የዴሞክራሲ ምህዳሩ ከተከፈተ በኋላ በሀገሪቱ የሚደረገው የመጀመሪያው ምርጫ ነው። ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ የነበሩት የፖለቲካ ማሻሻያዎች በሀገሪቱ ውስጥ ለወደፊቱ ዴሞክራሲ ይጠናከራል የሚል ተስፋን የሚያበረታቱ ነበሩ። ሆኖም ግን ተአማኒነት ያለው ምርጫ የመደረጉን ዕድል እና የሀገሪቱን የዴሞክራሲ ጉዞ የሚፈታተኑ ጉልህ አዳዲስ እና ነባር ተግዳሮቶች ተፈጥረዋል።

ለረጅም ጊዜ በጉጉት ሲጠበቅ የቆየው እና መጀመሪያ ላይ በ2012 ዓ.ም. እንዲደረግ ቀን ተቆርጦለት የነበረው ይህ ምርጫ ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ ተላልፎ የነበረ ሲሆን ይህም በትግራይ ክልል ወታደራዊ ግጭትን እና የምርጫ መታገድን አስከትሏል። ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ምክክሮችን ተከትሎ ግንቦት 12 ቀን የኢትዮጵያ ብሔራዊ መርጫ ቦርድ የምርጫው ቀን በድጋሚ ወደ ሰኔ 14 እንደሚተላለፍ አስታውቋል[2]። በተጨማሪም ምርጫው ከታገደበት ከትግራይ ክልል በተጨማሪ በጸጥታ ችግር፣ ከሎጂስቲክስ ጋር በተያያዙ አዳጋች ሁኔታዎች እና በመራጮች ምዝገዝባ መዘግየት የተነሳ ወደ 40 በሚጠጉ የምርጫ ክልሎች ድምጽ የመስጠት ሂደቱ እንደሚራዘም የኢትዮጵያ ብሔራዊ መርጫ ቦርድ ወስኗል። ከእነዚህም ውስጥ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ሱማሌ፣ ኦሮሚያ፣ አማራ፣ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች (ደ/ብ/ብ/ሕ) እና ሀረሪ ክልሎች ይገኙበታል። ሌሎች የምርጫ ክልሎችም በዚህ ዝርዝር ውስጥ ሊካተቱ ይችላሉ ብለው የሚጠብቁ አንዳንድ ባለድርሻ አካላት አሉ። በእነዚህ የምርጫ ክልሎች ውስጥ ድምጽ የመስጠቱ ሂደት መቼ ይከናወናል ብሎ እንደሚጠብቅ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መርጫ ቦርድ ያረጋገጠው ነገር የለም።

ጉዳዩን ይበልጥ ሰፋ አድርገን ስንመለከተውም ግልጽ ግጭቶችን የሚያስቆም እና በኢትዮጵያ የፖለቲካ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ወገኖችን በማሰባሰብ ሰላማዊ በሆነ መልኩ ለልዩነቶቻቸው መፍትሔዎችን እንዲያላልጉ የሚያስችል ብሔራዊ ውይይት በቀጣይ ይኖራል የሚል ተስፋ እንዳላቸው በርካታ አስተያየት ሰጪዎች ለተልዕኮው ገልጸዋል። ተልዕኮው ያነጋገራቸው አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎችም የምርጫው ሂደት በሀገሪቱ ያለውን ዴሞክራሲ መለኪያ እንደሚሆን ይገልጻሉ። ይህም ማለት በአፍሪካ ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎች የሚመሩባቸውን መርሆዎች በሚመለከተው የአፍሪካ ህብረት ድንጋጌ እንዲሁም ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው በርካታ ሌሎች ዓለም አቀፍ ሰነዶች መሰረት ወቅቱን የጠበቀ እና ተአማኒነት ያለው ምርጫ ለማከናወን ሀገሪቱ ያላትን ቁርጠኝነት የሚለካ ይሆናል ማለት ነው።

### የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወንበሮች




1 የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫ ጋር ጎን ለጎን ይከናወናል።

2 በተጨማሪም በቻርተር የሚተዳደሩት የአዲስ አበባ እና የድሬ ዳዋ ከተሞች የከተማ ምክር ቤት ምርጫዎች መጀመሪያ ላይ ታቅዶ እንደነበረው አንድ ሳምንት ቆይቶ ሳይሆን ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ከክልል ምክር ቤት መርጫዎች ጋር በተመሳሳይ ጊዜ እንደሚከናወን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ገልጿል።

## የሕግ ማእቀፍ እና በምርጫ ሂደት የሚነሱ አለመግባባቶች አፈታት፦

ምርጫ የሚከናወንበትን መንገድ በተመለከተ ከ2010 ዓ.ም. ጀምሮ በተደረጉት የሕግ ማሻሻያዎች ጠቅለል ባለ መልኩ ደስተኛ እንደሆኑ አስተያየት ሰጪዎች የሚገልጹ ሲሆን አብዛኞዎቹም በዚህ ረገድ የሕግና ፍትህ ጉዳዮች አማካሪ ጉባኤ ያደረገውን አስተዋጽኦ ይጠቅሳሉ።[3] ሆኖም ግን በአዲሱ የምርጫ ሕግ አተገባበር ላይ ዝርዝር መመሪያ ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ አንዳንድ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መመሪያዎች ገና አልወጡም።[4]

ፍርድ ቤቶች ከምርጫ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚዳኙባቸውን የሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ደንቦች የሚመለከተውን የፍርድ ቤት ደንብ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አላጸደቀውም። ይህ ሰነድ ፍርድ ቤቶች በምርጫ ሂደት የሚነሱ አለመግባባቶች ላይ ፈጣን እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ዳኝነት መስጠታቸውን ለማረጋገጥ የተረቀቀ እና ከምርጫ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ከመደበኛ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ደንቦች ውጭ የሚያደርግ ሲሆን ያለዚያ እነዚህ መደበኛ ደንቦች ጉዳዮች ከዓመት በላይ ጊዜ እንዲወስዱ የሚፈቅዱ ናቸው። ተልዕኮው ያነጋገራቸው አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች አንዳንድ የክስ ሂደቶችን ለማዘግየት ጥረት አድርጓል በማለት በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት እና በዐቃቤ ሕግ አገልግሎቶች ላይ ትችት የሰነዘሩ ሲሆን በተደጋጋሚ የሚቀርቡ የቴክኒክ አቤቱታዎች እና የተለዋጭ ቀጠሮ ጥያቄዎችም ለዚህ ማስረጃ ናቸው ብለዋል።[5]

የግንቦት ወር አጋማሽ ላይ ሁለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውሳኔዎች በጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጡ ውሳኔዎች ተሽረዋል። በአንደኛው ጉዳይ በእስር ላይ በመሆናቸው የተነሳ መመዝገብ ተከልክለው የነበሩ አራት የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፖለቲካ ፓርቲ ዕጩ አባላትን እንዲመዘግብ ፍርድ ቤቱ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ትእዛዝ የሰጠ ሲሆን እነዚህ አራት ዕጩ አባላት መጀመሪያ ላይ ያቀረቡት ይግባኝ ውድቅ ተደርጎባቸው ነበር። ይህን ተከትሎም ፓርቲው የሰበር ውሳኔው እንዲፈጸምለት ወደ ፍርድ ቤት የተመለሰ ሲሆን ውሳኔውን ማክበር የሕግ ግዴታ እና ሊያመልጡት የማይቻል ነው። በሁለተኛው ጉዳይ በክልሉ ሕገ መንግስት መሰረት ከሀረሪ ክልል ድንበር ውጭ ያሉ የሀረሪ ተወላጆች በሀረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ምርጫ ላይ ድምጽ እንዲሰጡ እንዲያመቻች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን የሚያዝ አስቀድሞ የተሰጠ ውሳኔን በመቃወም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያቀረበውን ይግባኝ ፍርድ ቤቱ ውድቅ አድርጓል።

አፈጻጸማቸውን ለማሻሻል በመሠራት ላይ ያሉ ሥራዎች ቢኖሩም በምርጫ ሂደት የሚነሱ አለመግባባቶች አፈታት ሥርዓቱ ሌሎች ክፍሎች በተሟላ መልኩ የሚሰሩ አይደሉም። በምርጫ አአስተዳደሩ ውስጥ ያሉት የተሻሻሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በምርጫ ጣቢያ ደረጃ አይንቀሳቀሱም እንዲሁም በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች በምርጫ ክልል እና በክልል ደረጃም ጭምር አይንቀሳቀሱም። የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት እና ፎረሞች በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች በንቃት በመንቀሳቀስ ላይ ቢሆኑም የሚያስመዘግቡት ስኬት የተበጣጠሰ ነው እንዲሁም የሚያስገኙት ውጤት ወጥነት የለውም።[6] በሱማሌ ክልል ከመራጮች ምዝገባ ጋር ተያይዞ የቀረቡ ቅሬታዎችን ተከትሎ አሥር አባላት ያሉት ጊዜያዊ አጣሪ ጉባኤ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተቋቋመ ሲሆን ይህም በአዎንታዊነት የሚጠቀስ ነው። ነገር ግን በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ተመሳሳይ ቅሬታዎች በዚህ መልኩ አይስተናገዱም።

3 አማካሪ ጉባኤው ካስጀመራቸው አዳዲስ ሕጎች ውስጥ የሲቪል መህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ፤ የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ፤ የተሻሻለው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን አዋጅ፤ እና የመገናኛ ብዙሀን አዋጁ ይገኙበታል።

4 በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ገና ካልተጠናቀቁት እና ካልጸደቁት መመሪያዎች ውስጥ የድምጽ አሰጣጥ እና አቆጣጠርን፤ በምርጫ ሂደት የሚነሱ አለግባባቶችን፤ እና ተንቀሳቃሽ የምርጫ ጣቢያዎችን የሚመለከቱ መመሪያዎች ይገኙበታል።

5 የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ ፕሬዝዳንት የሆኑት አቶ እስክንድር ነጋ እና የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮነግረስ (ኦ.ፌ.ኮ.) አባል የሆኑት አቶ ጀዋር መሀመድ ሁለቱም በተለያዩ ጉዳዮች ሰኔ 25 ቀን 2012 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ፍርድ ቤት ቀርበዋል። የምስክሮችን ማንነት ከመደበቅ ጋር የተያያዙ የቅድመ-ክርክር አቤቱታዎች በሁለቱም ጉዳዮች ላይ እስከ አሁን ድረስ ለፍርድ ቤቶቹ መቅረባቸው የቀጠለ ሲሆን በተደጋጋሚ ተለዋጭ ቀጠሮዎች ተሰጥተዋል።

6 የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቱ ሕጉን ለማስፈጸም እንዲያግዝ እና እንደ አማራጭ የግጭት አፈታት ዘዴ እንዲያገለግል በምርጫ አወጁ መሠረት በፖለቲካ ፓርቲዎች የተቋቋመ ነው።

## የምርጫ አስተዳደር፡-

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በጥቅሉ የህዝብ እምነት ያለው ሲሆን ተልዕኮው ያነጋገራቸው አብዛኛዎቹ አስተያየት ሰጪዎች የምርጫው ሂደት በመከናወን ላይ የሚገኘው ከመደበኛው ወጣ ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ እንደሆነ ይገነዘባሉ። ነገር ግን አስተያየት ሰጪዎቹ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የክልል ጽ/ቤቶች ላይ በሙሉ እምነት አላቸው ለማለት አይቻልም።

ምንም እንኳን የዕጩዎች ምዝገባ ሂደት ከሁለት ወራት በላይ በፊት የተጠናቀቀ ቢሆንም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በእያንዳንዱ የምርጫ ክልል ያሉትን ዕጩዎች ዝርዝር እስከ አሁን ድረስ ይፋ አላደረገም። የግንቦት ወር አጋማሽ ላይ ራሳቸውን ያገለሉ ዕጩዎችን እና ሌሎች ለውጦችን የሚያሳይ ወቅታዊ የሆነ አጠቃላይ አሀዛዊ መረጃ ያወጣ ሲሆን ይህም በድምሩ 9,470 ዕጩዎች በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሁም በክልል ምክር ቤት ምርጫዎች ላይ እንደሚወዳደሩ ያሳያል። አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች በአብዛኛዎቹ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ክልሎች እንዲሁም በተለይም ደግሞ በኦሮሚያ ምርጫው ፉክክር የሌለበት ይሆናል ብለው ይጠብቃሉ።

ግንቦት 7 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በአሁኑ ወቅት የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር 36,245,444 መሆናቸውን የሚገልጽ ቅታዊ መረጃ ያወጣ ሲሆን ይህም በተራዘመው የመራጮች ምዝገባ ወቅት የተከናወኑ ተጨማሪ ምዝገባዎችን የሚያንጸባርቅ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተከናወነ የህዝብ ቆጠራ ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ ውስጥ በእያንዳንዱ የምርጫ ክልል ውስጥ ያሉትን ለመምረጥ ብቁ የሆኑ ሰዎች ብዛት በተመለከተ ያሉት ግምቶች ትክክለኛውን ቁጥር የሚያንጸባርቁ አይደሉም። በእያንዳንዱ የምርጫ ክልል ውስጥ በተመዘገቡ መራጮች መጠን መካከል ልዩነቶች መኖራቸው እና በአንዳንድ የምርጫ ክልሎች ውስጥ በተጨባጭ የተመዘገቡት መራጮች ብዛት ይኖራሉ ተብሎ ከተተነበየው ለመምረጥ ብቁ የሆኑ ሰዎች ቁጥር በላይ መሆኑ በተለይም ደግሞ የምርጫ ክልሎችን መልሶ የማካለል እና ድንበር የማካለል ሥራ ለመጨረሻ ጊዜ የተከናወነው እ.ኤ.አ. በ1995 በመሆኑ ከድምጽ አሰጣጡ እኩልነት ጋር በተያያዘ አንዳንድ ስጋቶችን የሚፈጥር ነው። በተጨማሪም አስቀድመው ከነበሩት 138,655 የምርጫ ሠራተኞች በተጨማሪ ሌሎች 106,345 ሰዎችን በምርጫ ሠራተኛነት እንዲያገለግሉ ለመቅጠር ዕቅድ እንዳለው ግንቦት 12 ቀን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አስታውቋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንደሚለው ከሆነ ሰኔ 4 ቀን የምርጫ ሠራተኞች በምርጫ ቀን ተግባራዊ በሚደረጉ ሥነ-ሥርዓቶች ዙሪያ በአራት ደረጃ የተከፋፈለ ስልጠና መውሰድ ይጀምራሉ። በምርጫው ቀን ማቴሪያሎችን ለማከፋፈል 9,000 ተሽከርካሪዎች እንደሚያስፈልጉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሚገምት ሲሆን ይህም ከሰኔ 9 እስከ ሰኔ 11 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በሦስት ደረጃዎች ተከፋፍሎ የሚሰራጭ ይሆናል። ማቴሪያሎች በመጀመሪያ ወደ 20 የከተማ ማዕከላት ይጓጓዛሉ፣ ከዚያም ወደ ምርጫ ክልሎች ይወሰዳሉ፣ ከዚያም ሰኔ 8 ቀን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይፋ በሚደረገው መረጃ መሠረት በመጨረሻ ወደ ምርጫ ጣቢያዎች ይወሰዳሉ። በትግራይ ውስጥ ካሉት በስተቀር በሁሉም የምርጫ ክልሎች ውስጥ ምርጫ የሚካሄድ ቢሆን ኖሮ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ 49,407 የምርጫ ጣቢያዎች ይኖራሉ ብሎ ይጠብቅ ነበር። በአሁኑ ወቅት በ38 የምርጫ ክልሎች የምርጫው ጊዜ ከመተላለፉ ጋር ተያይዞ ግን በምርጫው ቀን በተጨባጭ የሚኖሩት የምርጫ ጣቢያዎች ብዛት ከዚያ ያነሰ ይሆናል። የክልል መንግስታት ማቴሪያሎችን የማጓጓዙን ሥራ በማመቻቸት እገዛ እንዲያደርጉ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጥያቄ ያቀረበ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ የሚያደርጉት ትብብር የተሻሻለ መሆኑን አረጋግጧል። የሰኔ ወር አጋማሽ የክረምቱ ዝናብ ለሚጀምርበት ጊዜ የተቃረበ መሆኑ ፈታኝ ተግዳሮት ይሆናል ተብሎ የሚገመት ሲሆን በምእራብ፣ በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ የኢትዮጵያ ክፍሎች በጣም ጎጂ ውጤቶችን ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ይጠበቃል።



**36,245,444**
መራጮች ተመዝግበዋል
(እስከ ግንቦት 7)



**46,088**
የምርጫ ጣቢያዎች
ለኖሩ ይችላሉ



**245,000**
የምርጫ ሠራተኞች ይኖራሉ
ተብሎ ይገመታል

## የፖለቲካ ፓርቲዎች እና በምርጫ ቅስቀሳ ዙሪያ ያለው ከባቢ ሁኔታ፡-

ምንም እንኳን የምርጫ ቅስቀሳ በየካቲት ወር በይፋ የተጀመረ ቢሆንም የእውነት መታየት የጀመረው ግን ባለፈው ወር ነው። በጣም ጎልተው የሚታዩት ተፎካካሪዎች ብልጽግና ፓርቲ እና የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ሲሆኑ የምርጫ ቅስቀሳ ምስሎቻቸው በዋና ከተማው ይታያሉ እንዲሁም በሌሎች ዋና ዋና ከተሞች እና ዋና መንገዶች ላይ እንደሚታዩ ዘገባዎች ይገልጻሉ። ከመራጮቻቸው ጋር ፊት ለፊት መገናኘት ተመራጭ የምርጫ ቅስቀሳ ዘዴያቸው እንደሆነ አብዛኛዎቹ ፓርቲዎች ይገልጻሉ። የተስተካከለ የመጫወቻ ሜዳ ስለመኖሩ ስጋቶች በሰፊው ይስተዋላሉ እንዲሁም ስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ የመንግስትን ሀብት ያለአግባብ ጥቅም ላይ በማዋል ላይ ነው የሚሉ ወቀሳዎች መኖራቸውን ተልዕኮው ያነጋገራቸው በርካታ አስተያየት ሰጪዎች እና አንዳንድ የመገናኛ ብዙሀን በአጽንኦት ገልጸዋል።

በምርጫው ለሚወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግስት በቀጥታ የሚሰጡ ድጎማዎች በሁለት ዙር ተከፋፍለው የተሰራጩ ሲሆን ይህም በድምሩ ወደ 98 ሚሊዮን ብር (2.25 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር) አከባቢ ነበር። ከሚያዝያ 11 ጀምሮም ከአጠቃላይ የገንዘብ ድጋፉ ውስጥ አሩቡ ለሁሉም ተሳታፊዎች እኩል ተከፋፍሏል። ከተቀረው ሦስት አራተኛ የገንዘብ ድጋፍ ውስጥ ተፎካካሪዎቹ የሚያገኙት ድርሻ ከግንቦት ወር ሦስተኛው ሳምንት ጀምሮ የተከፈለ ሲሆን ይህም የተከናወነው በውስጣቸው የያዟቸውን ሴቶች እና የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ብዛት ጨምሮ ተፎካካሪዎቹ ያሰማሯቸውን ዕጩዎች ብዛት እንዲሁም በሥራ አስፈጻሚ ኃላፊነት ቦታዎቻቸው ላይ ያሏቸውን ሴቶች ብዛት መሠረት በማድረግ ነው። ብልጽግና ፓርቲ ከአጠቃላይ ገንዘቡ ውስጥ ትልቁን ድርሻ (23.2 ሚሊዮን ብር ወይም 530,000 የአሜሪካ ዶላር) ያገኘ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ኢዜማ ደግሞ የዚያን ግማሽ የሚጠጋ ገንዘብ አግኝቷል። የገንዘብ ድጋፉ ዘግይቶ የተከፋፈለ መሆኑ ስኬታማ በሆነ መልኩ የምርጫ ቅስቀሳዎችን የማቀድ እና ተግባራዊ የማድረግ ችሎታቸውን እንደጎዳው በርካታ ፓርቲዎች ለተልዕኮው ገልጸዋል። ምንም እንኳን ሕጋዊ መብታቸው ቢሆንም በግላቸው በምርጫው ላይ ለሚወደደሩ እጩዎች ከመንግስት የተሰጠ ምንም የገንዘብ ድጋፍ የለም። ለምርጫ ቅስቀሳ በሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ ግልጽነት ዙሪያ ያሉት እርምጃዎች ዝቅተኛ ናቸው እንዲሁም የሚያካትቱት ከመንግስት በተገኘው የገንዘብ ድጋፍ የተሸፈኑ ወጪዎችን በተመለከተ ብቻ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታን እና በፖለቲካ ፓርቲዎች ሂሳብ ላይ የሚደረጉ ዓመታዊ ኦዲቶችን ነው።

በአንዳንድ የምርጫ ክልሎች ውስጥ ያለው አስጊ የጸጥታ ሁኔታ በነጻነት ቅስቀሳ የማድረግ መብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። ከዚህ ጎን ለጎን ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በደጋፊዎቻቸው እና በዕጩዎቻቸው ላይ ስለሚደርሰው ማስፈራራት እና ትንኮሳ ቅሬታዎችን አቅርበዋል። ግንቦት 19 ቀን የተካሄደ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ኢዜማ በአማራ እና በደ/ብ/ብ/ሕ ክልሎች በሚገኙ በርካታ የምርጫ ክልሎች ውስጥ ዕጩዎቹ እና አባላቱ እስር እና መጉላላት እየደረሰባቸው እንደሆነ ገልጿል። የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄም (አብን) እንዲሁ አባላቱ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና በድሬ ዳዋ እስር እንደደረሰባቸው ለተልዕኮው ገልጿል። በተጨማሪም እናት ፓርቲ ኦሮሚያን፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝን እና ድሬ ዳዋን ጨምሮ በተለያዩ ክልሎች ውስጥ ተከታዮቹ ትንኮሳዎች እና ዛቻዎች እንደደረሱባቸው ግንቦት 18 በይፋ ገልጿል።



**46 ከ 53**

የተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች



**9,470**

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና
የክልል ምክር ቤት ዕጩዎች

## ከምርጫ ጋር በተያያዘ ያለው የጸጥታ ሁኔታ፡-

በርካታ ክልሎች ውስጥ ያለው አጠቃላይ የጸጥታ ሁኔታ እና የቀጠለው ውጥረት ሰኔ 14 ቀን ከሚካሄደው ምርጫ አስቀድመው ባለድርሻ አካላት ከሚዘረዝሯቸው ስጋቶች ውስጥ ግንባር ቀደሙን ቦታ ይይዛሉ። ከጸጥታ ጋር የተያያዙ ክስተቶች ብዛት እና ክብደት እየጨመረ መምጣቱን እና ከእነዚህም ውስጥ በርካታዎቹ በቀጥታ በምርጫው ላይ ያነጣጠሩ መሆናቸውን ተልዕኮው ያነጋገራቸው አስተያየት ሰጪዎች ጠቅሰዋል። ዘገባዎች እንደሚጠቁሙት ከሆነ ሂደቱ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በአማራ ክልል ውስጥ የሚገኙትን የኦሮሚያ ልዩ ዞኖች እና የጎንደር ዞንን ጨምሮ 20 የምርጫ ጣቢያዎች ጥቃት ተፈጽሞባቸዋል። በሱማሌ፣ በደ/ብ/ብ/ሕ፣ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች ውስጥ እንዲሁም በድሬ ዳዋ በዕጩዎች፣ ለመመዝገብ ጥረት ባደረጉ መራጮች፣ በአካባቢ የምርጫ አስፈጻሚዎች እና በሸማግሌዎች ላይ መጠነ ሰፊ ማሸማቀቅ፣ ጫና፣ አግባብ ያልሆነ እስር እና መጉላላት መድረሱ ለተልዕኮው ተገልጾለታል። ግጭቶችን ለመቀነስ እና ለመከላከል ሰላማዊ ጥረቶች በመደረግ ላይ ያሉ ቢሆንም የሀብት ውስንነት መኖሩ እና በፌዴራል እና በክልል ወይም በሌሎች የጸጥታ ኃይሎች መካከል የስልጣን መደራረብ መኖሩ የእርምጃዎቹን ውጤታማነት ውስን አድርጎታል እንዲሁም የህዝቡን ፍርሀት ሁልጊዜም አይቀንሱም። በክልል ደረጃ ያሉ የጸጥታ ተዋንያን በሂደቱ ውስጥ መሳተፋቸው የተወሰነ ዋስትና የሚሰጥ ቢሆንም ገለልተኛ ስለመሆናቸው ጥየቄዎችን ያስነሳል። የኃይሎቹ ኃላፊነት በዝርዝር ያለመቀመጡ ግራ መጋባትን ሊፈጥር እና የፖለቲካ መጠቀሚያ የሚሆኑበትን ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል። የምርጫ ሂደቱ ከፍተኛ የጸጥታ ቁጥጥር ያጠላበት መሆኑ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚገኙ መራጮች በምርጫው እንዳይሳተፉ የሚያደርግ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል የሚለውን ስጋት ከፍ የሚያደርግ ነው። በተመሳሳይ መልኩ ተልዕኮው ያነጋገራቸው አብዛኛዎቹ አአስተያየት ሰጪዎች የጸጥታ ችግሮች ወይም ግጭቶች ከምርጫው በፊት፣ በምርጫው ቀን ወይም ኪዚያ በኋላ ወዲያውኑ በከፍተኛ ሁኔታ ይባባሳሉ ብለው አይጠብቁም።

## ኮቪድ-19 እና የምርጫው ሂደት፡-

የጤና ፕሮቶኮሎች ተግባራዊ በማድረግ እና በመከተለል ረገድ ያለው ሁኔታ በአጠቃላይ ያልተመጣጠነ ሆኖ ቆይቷል። የምርጫ ቅስቀሳ ዝግጅቶች ላይ ተሳታፊዎች ማስክ ሳያደርጉ የተገኙባቸው አጋጣሚዎች እንደነበሩ በመገናኛ ብዙሀን ታይቷል እንዲሁም በአንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ተገልጿል። ምርጫው መራዘሙን ተከትሎ ባለሥልጣን አካላት ደህንነቱ አስተማማኝ የሆነ የድምጽ አሰጣጥ ሂደት መኖሩን ለማረጋገጥ የሕግ ማዕቀፉን አሻሽለዋል። በየካቲት ወር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሁሉም የሂደቱ ደረጃዎች ላይ ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸውን እርምጃዎች በተመለከተ ለምርጫ አስፈጻሚዎች እና ባለድርሻ አካላት መመሪያ የሚሰጠውን “በምርጫ ወቅት የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመቀነስ የሚያግዙ እርምጃዎችን ማክበርን የሚመለከት መመሪያ ቁጥር 9/2013” አውጥቷል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሠራተኞች፣ ዕጩዎች፣ የፓርቲ ወይም የዕጩ ወኪሎች፣ የምርጫ ታዛቢዎች፣ የመራጮች ትምህርት ሰጪዎች፣ ጋዜጠኞች እና አግባብነት ያላቸው ተሳታፊዎች በሙሉ ከምርጫ ጋር ግንኙነት ያላቸው እንቅስቃሴዎች ላይ ሁሉ ማስኮችን ወይም ሌሎች የፊት መሸፈኛዎችን ማድረግን ጨምሮ የጤና ፕሮቶኮሎችን መከተል አለባቸው።[7] በተጨማሪም መመሪያው የምርጫው ቀን ላይ የድምጽ መስጫ ክፍሎች በታዛቢዎች፣ በፓርቲ ወይም በዕጩ ወኪሎች እና በመገናኛ ብዙሀን ተወካዮች ከመጠን በላይ እንዳይጨናነቁ ገደብ የሚያስቀምጡ ድንጋጌዎች አሉት። ዕድሜያቸው ከ60 ዓመት በላይ እንደሆኑ ግለሰቦች፣ እንደ ነፍሰጡር ሴቶች፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች እና ለኮቪድ-19 ተጋላጭ የሚያደርጓቸው ችግሮች ያሉባቸው ሰዎች ያሉ ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች ልዩ የመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ ድንጋጌዎች ተዘጋጅተውላቸዋል። ከላይ የተገለጹትን ግዴታዎች ያለማክበር ወደ ማናቸውም የምርጫ ስፍራዎች እንዳይገቡ ወደ መከልከል ሊያመራ እንዲሁም በህዝብ ጤና እና በወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት መቀጣትን ሊያስከትል ይችላል። በተጨማሪም በፖለቲካ ፓርቲዎች የተመረጡ ዕጩዎች ፊርማ እንዲሰበስቡ የሚጠይቀውን ድንጋጌ የሚያስቀር ማሻሻያ በምርጫ አአዋጁ ላይ በየካቲት ወር ተደርጎ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጸድቋል። ከዚህም በተጨማሪ በግላቸው የሚወዳደሩ ዕጩዎች ማቅረብ ያለባቸውን ፊርማዎች ብዛት 2,500 እንዲሁም የአካል ጉዳት ያለባቸው ዕጩዎች ማቅረብ ያለባቸውን ደግሞ 1,500 በማድረግ በግማሽ ቀንሷል።

7 በምርጫ ስፍራዎች እና እንቅስቃሴዎች ላይ የተመደቡ የጸጥታ ሰራተኞች የአሠራር እና የሥነ-ምግባር ደንብ መመሪያ ቁጥር 12/2013 የምርጫ ጸጥታ አገልግሎት ሰጪዎች እና ሠራተኞቻቸው ሊወስዷቸው የሚገቡ እርምጃዎችን እና ያሉባቸውን ግዴታዎች የሚዘረዝር ነው። አብዛኛዎቹ መመሪያዎች የምርጫውን ቀን የሚመለከቱ ናቸው።

## የተገፉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ማካተት፡-

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባወጣቸው መረጃዎች መሠረት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሁም ለክልል ምክር ቤት ምርጫዎች ከሚወዳደሩት ዕጩዎች ውስጥ ሴቶች 21 በመቶውን (ከ9,470 ውስጥ 1,976) ይይዛሉ። በ2007 ዓ.ም. ለመጨረሻ ጊዜ የተደረገው ምርጫ ላይ ከነበሩት አጠቃላይ ዕጩዎች ውስጥ 29 በመቶው ሴቶች ነበሩ። ይህ የሴት ዕጩዎች ድርሻ መቀነስ በተለይ በአጠቃላይ ያለው የዕጩዎች ቁጥር በግማሽ ከመጨመሩ አንጻር ሲታይ የሚያስደንቅ ነው። በግላቸው ከሚወደዳደሩት 143 ዕጩዎች ውስጥ ያሉት አምስት ሴቶች ብቻ ናቸው እንዲሁም ምንም ሴት ዕጩ ያላቀረቡ በርካታ ፓርቲዎች አሉ። ከብልጽግና ፓርቲ ዕጩዎች ውስጥ ከ40 በመቶ በላይ የሚሆኑት ሴቶች ሲሆኑ ይህም ከሁሉም ፓርቲዎች በላይ የጾታ ሚዛኑን የጠበቀ የዕጩዎች ስብስብ ያለው ፓርቲ ያደርገዋል። ሴት ዕጩዎችን ይበልጥ ለማስመዝገብ ፈልገው የነበረ ቢሆንም የጸጥታ ሁኔታው እና ሴት የተቃዋሚ ፓርቲ ዕጩዎች የሚያጋጥሟቸው የተለዩ ተግዳሮቶች በርካታ ሴቶችን እንዳይወዳደሩ ተጽዕኖ እንዳሳደረባቸው አንዳንድ ፓርቲዎች ይገልጻሉ። ሴት የተቃዋሚ ዕጩዎች ራሳቸውን ከምርጫው እንዲያገሉ ወይም የፖለቲካ ግንኙነታቸውን እንዲቀይሩ ዛቻዎች እንደሚደርሱባቸው ወይም ጫና እንደሚደረግባቸው የሚገልጹ በርካታ ዘገባዎች ለተልዕኮው ደርሰውታል።



**1,976 (21 በመቶ)**
**ሴት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የክልል ምክር ቤት ዕጩዎች**

የአካል ጉዳት ካለባቸው ሰዎች ጋር በተያያዘ በሕግ ማዕቀፉ ውስጥ አዎንታዊ ለውጦች እንዳሉ እንዲሁም በጉዳዩ ዙሪያ ያለው ይፋዊ አመለካከት እንደተለወጠ በርካታ አስተያየት ሰጪዎች የገለጹ ቢሆንም እነዚህን ለውጦች ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ግን ያለው መሻሻል ውስን በመሆኑ የምርጫውን ሂደት የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ይበልጥ ተደራሽ በማድረግ ረገድ የመጣው ለውጥ በጣም ትንሽ ነው። በርካታ የተለያዩ የመራጮች ማስተማሪያ እና የቅስቀሳ ማቴሪያሎችን በብሬል ወይም በኦዲዮ-ቪዡዋል ቅርጸት ማዘጋጀት እና ህንጻዎች የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ አሁንም አስቸኳይ እና አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ነው። በፖለቲካ ፓርቲዎች ተመርጠው ከቀረቡት ዕጩዎች ውስጥ 95 ዕጩዎች ራሳቸውን የአካል ጉዳት ያለበት ሰው ብለው የሚገልጹ ናቸው።

የትምህርት ቤቶች የዕረፍት ወቅት የግንቦት ወር መጨረሻ ላይ የሚጀምር ከመሆኑ አንጻር ለመጨረሻ ጊዜ የተደረገው የምርጫ ማራዘሚያ በርካታ ተማሪዎች በመኖሪያ አካባቢያቸው ባለ የምርጫ ክልል ድምጻቸውን እንዲሰጡ የሚያስችል ይሆናል። ከዚህ ጎን ለጎን የወጣት መራጮችን ተሳትፎ ለማሳደግ በባለድርሻ አካላት በቂ ሥራዎች ባለመሠራታቸው የተነሳ ወጣት መራጮች በአጠቃላይ ግድ የለሽ ሆነዋል። በተጨማሪም አንድ ብቻ ለወንበር የሚወዳደር ዕጩ ያላቸው እና ፉክክር የማይኖርባቸው በርካታ የምርጫ ክልሎች ይኖሩታል ተብሎ በሚጠበቀው በኦሮሚያ ክልል ውስጥም እንዲሁ ከወጣቶች ተሳትፎ ጋር በተያያዘ የተነሱ ስጋቶች አሉ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ወደ 2 ሚሊዮን የሚጠጉ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች እንዳሉ ዓለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት (IOM) በጥር ወር 2013 ዓ.ም. ሪፖርት አድርጓል።[8] በመመሪያ ቁጥር 13/2013 መሠረት በሱማሌ፣ በኦሮሚያ፣ በአፋር፣ በደ/ብ/ብ/ሕ ክልሎች እንዲሁም ምንአልባትም በድሬ ዳዋ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች በሚገኙባቸው ስፍራዎች ልዩ የምርጫ ጣቢያዎችን ለማቋቋም ዕቅድ እንዳለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለተልዕኮው አሳውቋል። እነዚህ ስፍራዎች ከዚህ ቀደም በነበሩ ግጭቶች የተነሳ ለተፈናቀሉ መራጮች አገልግሎት ይሰጣሉ ተብሎ ይጠበቃል። በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ በማህበረሰቦች መካከል በተፈጠሩ እና በሂደት ላይ ባሉ ግጭቶች የተነሳ በአንጻሩ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተፈናቀሉ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችን ፍላጎቶች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንዳያሟላ ከሎጂስቲክስ እና ከጸጥታ ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶች እንቅፋት እንደሆኑበት ተገልጿል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንደገለጸው ከሆነ የሀገር ውስጥ ተፈናቀዮችን በተመለከተ የቋንቋ ፍላጎቶቻቸውን ጨምሮ የተሟላ መረጃ ያለመኖሩ በዚህ ረገድ የሚያደርጋቸውን ጥረቶች ፈታኝ አድርገውታል።

---

8 https://dtm.iom.int/ethiopia

ቢያንስ ሁለት የክልል የፖለቲካ ፓርቲዎች ሀገር አቀፍ ሽፋን ያላቸው ተፎካካሪዎቻቸው ለልዩ የምርጫ ክልል ወንበሮች የመወዳደር መብት የላቸውም በማለት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን እነዚህ ወንበሮች በአናሳ ብሔሮች እና ቋንቋዎች ለተቋቋሙ ፓርቲዎች የተያዙ ናቸው ብለዋል።[9] ከዚህ ጎን ለጎን የቋንቋ ችግር እና አግባብነት ያላቸው የምርጫ ማቴሪያሎችን ከአማርኛ እና በቅርቡ የሥራ ቋንቋ ከሆኑት ሌሎች አራት ቋንቋዎች ውጭ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች ለመተርጎም የሚደረጉት ጥረቶች ውስን መሆናቸው አንዳንድ ብሔሮች እና ቋንቋዎች ያሏቸው ማህበረሰቦች በተለይም ደግሞ በደ/ብ/ብ/ሕ ክልል በምርጫው ሂደት ውስጥ እንዳይሳተፉ እንቅፋት እንደሆኑ ባለድርሻ አካላት ጠቅሰዋል።

## የሲቪል ማህበረሰብ ምህዳር እና የዜጎች ተሳትፎ፡-

በጥቅሉ የሲቪል ማህበረሰብ አዋጅ ቁጥር 1113/2011 መውጣቱን ተከትሎ የሲቪል ማህበረሰብ ምህዳሩ ክፍት በመሆኑን ሲቪሉ ማህበረሰብ በደስታ ተቀብሎታል። ግንቦት 13 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዘጠኝ ተጨማሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምርጫውን እንዲታዘቡ የተመዘገቡ መሆኑን ያስታወቀ ሲሆን ይህም በድምሩ 45 የተለያዩ ድርጅቶች ተመዝግበዋል ማለት ነው። የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ጥምረት ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የመጡ 175 የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በስሩ ያሰባሰበ እና ትልቁ ገለልተኛ የዜጎች ምርጫ ታዛቢ እንቅስቃሴ ሲሆን 3,000 ታዛቢዎችን በማሰማራት በአጠቃላይ ካሉት የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ አሥር በመቶውን የመሸፈን ዕቅድ አለው።

ከሲቪል ማህበረሰብ የመጡ አስተያየት ሰጪዎች ከምርጫ አስተዳደሩ ጋር ስላላቸው ግንኙነት አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ቢሆንም ዕውቅና ያገኙት ዘግይተው በመሆኑ መጠነ ሰፊ ትችት የተሰነዘረበትን የመራጮች ምዝገባን ጨምሮ ቁልፍ የሂደቱን ምዕራፎች ለመታዘብ ያልቻሉ መሆኑን በአጽንኦት ገልጸዋል። ግንቦት 15 በሲቪል ማህበረሰብ ፎረም ጠቅላላ ጉባዔ የጸደቀው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሥነ-ምግባር ደንብ በአባል ድርጅቶቹ የጸደቀ ሲሆን ይህም ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻ መሆንን እና ጣልቃ ያለመግባትን የማጠናከር ዓላማ ያለው የራስ-ቁጥጥር ዘዴን ተግባራዊ እንዲያደርጉ አባል ድርጅቶቹን የሚያስገድድ ነው። ተልዕኮው ያነጋገራቸው በርካታ አስተያየት ሰጪዎች እንደገለጹት ከሆነ የፖለቲካ ምህዳሩ ለዓመታት ተዘግቶ መቆየቱን ተከትሎ የሀብቶች ውስንነት እና የቴክኒክ አቅሞች ማነስ መኖሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ውጤታማነት አዳክሞታል። ምንም እንኳን ወደ 167 የሚጠጉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሀገሪቱ ዙሪያ የመራጮች እና የዜጎች ትምህርት እንቅስቃሴዎችን እንዲያከናውኑ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዕውቅና የተሰጣቸው ቢሆንም ከጂኦግራፊ፣ ከጸጥታ እና ከገንዘብ ጋር በተያያዙ ማነቆዎች የተነሳ ሽፋናቸው አሁንም ውስን ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ምርጫው መራዘሙ በርከት ያለ ቁጥር ያላቸው መራጮች ጋር እንድንደርስ ያስችለናል የሚል ተስፋ እንዳላቸው በርካታ ግሩፖች ገልጸዋል።

## መገናኛ ብዙሀን እና በመረጃ ዙሪያ ያለው ከባቢ ሁኔታ፡-

መገናኛ ብዙሀንን በሚያስተዳድረው የሕግ ማዕቀፍ ላይ መሻሻሎች መኖራቸው እና የመገናኛ ብዙሀን ባለሞያዎች ብዝሀነት በአጠቃላይ እያደገ መሆኑ አብዛኛዎቹ አስተያየት ሰጪዎች ዕውቅና የሰጡት ጉዳይ ነው። መጋቢት ወር መጨረሻ ላይ የታተመው አዲሱ የመገናኛ ብዙሀን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አዎንታዊ እርምጃ ተብሎ የተገለጸ ነበር እንዲሁም በርካታ ባለድርሻ አካላት ለኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለስልጣን የላቀ ነጻነትን የሚያቀዳጅ ይሆናል ብለው የሚጠብቁት ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ይመጣሉ ተብለው የሚጠበቁት እነዚህ ለውጦች ሰኔ 9 ቀን በይፋ ለሚያበቃው የምርጫ ቅስቀሳ መገናኛ ብዙሀን በሚሰጡት ሽፋን ላይ የሚኖራቸው ፋይዳ ውስን ነው።

የመገናኛ ብዙሀን መልክአ ምድሩ በፌዴራል እንዲሁም በክልል ደረጃ መንግስትን የሚደግፍ አቋም ያላቸው በርካታ የመንግስት እና የግል መገናኛ ብዙሀን የበላይነት የሰፈነበት ነው። የገቢ መቀነስ በግል መገናኛ ብዙሀን ላይ የሚኖረው ጫና እንዲጨምር ያደርጋል ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን እነዚህ የግል መገናኛ ብዙሀን በርካታዎቹ በማስታወቂያ ገበያው ውስጥ ጉልህ ድርሻ የሚይዙትን የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ትዕዛዝ ለማግኘት የሚፎካከሩ ናቸው።

9 ሁለቱም ቅሬታዎች የቀረቡት በመጋቢት ወር ነበር። በመርህ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም የምርጫ አዋጁ ፓርቲዎቹ በአናሳ ብሔሮች እና ቋንቋዎች ለተቋቋሙ ፓርቲዎች የተያዙ ናቸው ላሏቸው ወንበሮች ዕውቅና አይሰጥም። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በጉዳዩ ላይ ያወጣው መረጃ የለም።

## የጋዜጠኞች ደህንነት አሁንም በከፍተኛ ሁኔታ አሳሳቢ ነው፡-

ከጥር ወር ወዲህ ሁለት ጋዜጠኞች ህይወታቸውን ያጡ ሲሆን በርካታ ባልደረቦቻቸው እንደታሰሩ ከመገናኛ ብዙሀን የመጡ አስተያየት ሲዎች ገልጸዋል።[10] ጋዜጠኞች ላይ ማስፈራራት፣ ጫና እና ማጉላላት እየደረሰ እንደሆነ የሚገልጹ ዘገባዎች ከህዳር ወር 2013 ዓ.ም. ጀምሮ እንደጨመሩ ይነገራል። በርካታ ጋዜጠኞች እና መገናኛ ብዙሀንም በተፈጠረው ሁኔታ የተነሳ ራሳቸውን ሳንሱር በማድረግ ላይ ናቸው። በተጨማሪም የገለልተኛ መገናኛ ብዙሀን ተወካዮች የመንግስት መረጃ ተደራሽነት እየቀነሰባቸው እንደሆነ እና ይህም ዘገባዎችን የመስራት እና የማዘጋጀት አቅማቸውን ውስን እንዳደረገው ይገልጻሉ።

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በምርጫው ለሚወዳደሩት 46 የፖለቲካ ፓርቲዎች እና በግል ለሚወዳደሩ 143 ዕጩዎች 1,400 ነጻ የአየር ሠዓታትን መድበዋል። አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያላቸው የቴክኒክ አቅም ውስን በመሆኑ የተነሳ ከነጻ የአየር ሠዓቱ ውስጥ ወደ እኩብ ያህሉ ጥቅም ላይ ሳይውል ቀርቷል። የመገናኛ ብዙሀን ተቋማት ከፖለቲካ ፓርቲዎች የሚመጡ ይዘቶችን ከመሰራጨታቸው በፊት ተቀብለው የሚገመግሙባቸው የምርጫ ዴስኮችን ያዘጋጁ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ ተፎካካሪዎቹ ይዘቶቻቸው ላይ ማስተካከያ እንዲያደረርጉ ጥያቄ እንዳቀረቡ የገለጹ በርካታ የመገናኛ ብዙሀን ተቋማት አሉ። የመንግስት የሆውን የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንን፣ ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬትን፣ አሀዱ ቴሌቪዥንን፣ የአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽንን እና ኢትዮ ቲዩብን ጨምሮ በርካታ የመገናኛ ብዙሀን ተቋማት በተፎካካሪዎች መካከል የሚደረጉ ክርክሮችን ማዘጋጀታቸውን ቀጥለዋል። እነዚህ ዝግጅቶች ዕኩል ተደራሽ ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ ስጋቶች የነሳሉ፡- በስልጣን ላይ ያለው ብልጽግና ፓርቲ በፋና ቴሌቪዥን ከቀረቡት ዘጠኝ ክርክሮች ውስጥ በሁሉም ላይ የተጋበዘ ሲሆን ኢዜማ የተሳተፈው በአራቱ ላይ ነው እንዲሁም ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች እያንዳንዳቸው ከሁለት ጊዜ በላይ አልተሳተፉም።

የፖለቲካ ፓርቲዎች በኢንተርኔት ላይ የሚያደርጉት የምርጫ ቅስቀሳ ከምርጫው በፊት ባለው የመጨረሻ ወር ውስጥ መጨመሩን ተልዕኮው በማህበራዊ ትስስር ገጾች ላይ ካደረገው ስልታዊ ግምገማ ለማወቅ ተችሏል። የጠቅላይ ሚኒስትሩ የግል የፌስቡክ ገጽ ከፍተኛው የተከታዮች ቁጥር አለው እንዲሁም ብልጽግና ፓርቲ በአጠቃላይ ከፍተኛው የተጠቃሚ ተሳትፎ አለው። በተጨማሪም ኢዜማን፣ ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲን እና ነጻነት እና እኩልነት ፓርቲን ጨምሮ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ምንም እንኳን በአንጻሩ አነስ ያለ ቢሆንም ትኩረት በማግኘት ላይ ናቸው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድም ለምርጫ የሚደረጉ ዝግጅቶች የሚገኙበትን ሁኔታ በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ ለማሰራጨት ከጊዜ ወደ ጊዜ ማህበራዊ ሚድያን ይበልጥ እየተጠቀመ መጥቷል። የሀሰት መረጃ በማደግ ላይ ያለ ችግር ነው ተብሎ የሚታሰብ ቢሆንም በሀገሪቱ ውስጥ እየተከናወኑ የሚገኙት ጥቂት ገለልተኛ እውነታ የማጣራት ሥራዎች ብቻ ናቸው።

10 የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ስለ ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ አርአያ (ትግራይ ቴሌቪዥን) እና ሲሳይ ፊዳ (ኦቢኤን) ሞት በስፋት ዘግበዋል።

## ስለ ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት (IRI)፡-

በዓለም ዙሪያ ነፃነትን እና ዲሞክራሲን ለማስፋፋት የሚሰራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ነው። ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት የፖለቲካ ፓርቲዎችን የበለጠ ሃሳብን መሠረት ያደረጉ እና ምላሽ ሰጭ እንዲሆኑ ያስችላል፣ ዜጎች በመንግስት እቅድ ውስጥ እንዲሳተፉ ያግዛል እንዲሁም በፖለቲካው ሂደት ውስጥ የተገለሉ ቡድኖች ሚና እንዲጨምር ይሠራል። ኢ.ኤ.አ. ከ1983 ጀምሮ ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት በ60 ሀገራት ውስጥ 206 ምርጫዎችን በዓለም አቀፍ ታዛቢዎች ተልዕኮዎች እና ግምገማዎች አማካኝነት ተከታትሏል። ለበለጠ መረጃ www.iri.org ጎብኙ።

## ስለ ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲቲዩት (NDI)፡-

ኤን ዲ አይ የዴሞክራሲ ተቋማትን፣ ሂደቶችን፣ ደንቦችን እና እሴቶችን ለማጠናከር እና ለመጠበቅ እንዲሁም ሁሉም ሰው የተሻለ ጥራት ያለው ኑሮ የሚኖርበትን ሁኔታ ለማረጋገጥ በዓለም ዙሪያ በአጋርነት የሚሰራ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ መንግስታዊ ያልሆነ እና ከፖለቲካዊ ውግንና ነፃ የሆነ ተቋም ነው። የኤን ዲ አይ ራዕይ ዴሞክራሲ እና ነፃነት የሰፈኑበት እና ሁሉም ሰው ሰብዓዊ ክብሩ የሚጠበቀበት ዓለም ተፈጥሮ ማየት ነው። ላለፉት 38 ዓመታት ኤን ዲ አይ በ70 ሀገራት ውስጥ ከ250 በላይ የምርጫ ታዛቢ ተልእኮዎችን አካሂዷል። ለበለጠ መረጃ ይሚከተለውን ድረ ገፃችንን ይጎብኙ፡- www.ndi.org

ይህ ሥራ በናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲቲዩት/ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዩት በጋራ የሚሠራው ከዩናይትድ ስቴትስ የዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው።

የኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲቲዩት (IRI)/ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲቲዩት (NDI) የ2013 የኢትዮጵያን ምርጫ የመታዘብ ውስን ተልዕኮ


**International Republican Institute**

1225 Eye Street NW, Suite 800
Washington, DC 20005

info@iri.org

**National Democratic Institute**

455 Massachusetts Ave NW, 8th
Floor Washington, DC 20001

http://www.ndi.org/contact